የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

https://t.me/sirius_logistics

ቁጥር/ Ref.No. 4/0585/16
ቀን/Date የካቲት 12 2016

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈጸምባቸዉ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት
ለጉምሩክ መረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ማዕከል
ጉምሩክ ኮሚሽን

ጉዳዩ:- የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማሻሻያን ይመለከታል

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ታ/መ/ነ/921/16 ቀን 06/06/2016 ዓ.ም አምራች እና ገጣጣሚዎች ይበልጥ ተወዳዳሪ ሆነው ገቢ ምርቶችን በአገር ዉስጥ ለመተካት የሚደረገዉን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ በየጊዜው በመፈተሽ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተገቢው የታሪፍ ከለላ እንዲኖራቸው አንደሚደረግ ገልጾ በተወሰኑ ግብዓቶች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ ማሻሻያ አድርጓል፡፡

በመሆኑም ማሻሻያዉ ከየካቲት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተቀባይነት በሚያገኙ የጉምሩክ ዲክላራሲዮኖች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑ ታውቆ በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤቶች ጥንቃቄ በተሞላበት አግባብ ተፈጻሚ እንዲሆን እያሳሰበኩ ማሻሻያዉ በተቋሙ መረጃ ቋት /local share/ አድራሻ \\10.12.0.8 ላይ tariff classification and origin ሳጥን ዉስጥ **የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማሻሻያ የካቲት** 06.06.2016 በሚል ርዕስ የተጫነ መሆኑን እየገለጽኩ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፈዉን ማሻሻያ 4 (አራት) ገፅ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የተላከላችሁ መሆኑን አሳዉቃለሁ፡፡

በተጨማሪም በተደረገው ማሻሻያ ተራ ቁጥር 5 ላይ ከመገጣጠም ከፍ ባለ ደረጃ እሴት በመጨመር ወደ አምራችነት ሽግግር በማድረግ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን ለማበረታታት የተፈቀደው ማበረታቻ አፈፃፀምና ቁጥጥርን በተመለከተ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል አስፈላጊው እንዲፈፀም በዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.1

ግልባጭ:-
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ስሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
  ጉምሩክ ኮሚሽን
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለፌደራል ዋና ኦዲተር
- ለኢትዮጵያ ጉምሩክ አስተላላፊዎች የሙያ ማህበር
  አዲስ አበባ

ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ፋ፫መ/ኃ/፻፳፩/፲፮
Ref.No
ቀን 6/6/2016
Date

ለጉምሩክ ኮሚሽን
ሲዳስ አበባ

ጉዳዩ፡- <u>የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማሻሻያን ይመለከታል</u>፤

አምራች እና ገጣጣሚ ኢንዱስትሪዎች ይበልጥ ተወዳዳሪ ሆነው ገቢ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚደረገውን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ በየጊዜው በመፈተሽ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተገቢውን የታሪፍ ከለላ እንዲኖራቸው እንደሚደረግ ይታወቃል፡፡

በዚህም በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 153/2000 በአንቀጽ 3 የሽቀጦች አሰያየምና ምደባ የተሳሳተ ሆኖ ሲያገኘው ስህተቱ እንዲስተካከል እንዲያደርግ፣ በዓለም ዓቀፍ የተዋሀደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ክለሳ ሲደረግ ይህንኑ ተከትሎ የአሰያየም፣ የአመዳደብ እና የታሪፍ መጣኔ ማስተካከያ እንዲያደርግ እና ከታሪፍ ከለላ ጋር በተያያዘ ምክንያት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴሮችና ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የገቢና ወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ እንዲወሰን ወይም ማሻሻያ እንዲያደርግ ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው የሥልጣን ውክልና መሠረት የሚከተሉት ማሻሻያዎችና ማስተካከያዎች ተደርገዋል፡፡

1. ታሪፍ ቁጥር 1101.1000 በብሔራዊ ታሪፍ ቁጥር ተከፋፍሎ እንደሚከተው ተሻሽሏል፤

አንቀጽ (1)	የኤች ኤስ ኮድ (2)	የታሪፍ ቁጥር (3)	የዕቃው ዓይነት (4)	የመስፈሪያው አይነት (5)	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ (6)
11.01	1101.10		የስንዴ ወይም የአጃ ዱቄት፡- Wheat or meslin flour:		
		1101.1010	--- የስንዴ --- of Wheat	ኪ.ግ kg	25%
		1101.1090	--- ሌሎች --- Others	ኪ.ግ kg	15%

https://t.me/sirius_logistics

Ministry of Finance ARCHIVES 6

ስልክ
251-11-155 24 00, 22 66 98
251-11-155 00 81, 83 86 89

የ ፖ.ሣ.ቁ
P.O.BOX 1905,1037

ፋክስ/Fax
251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38

MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet
mofed.gov.et

Ethiopian Customs Commission Records Documentation ቁጥር 1 No 1

https://t.me/sirius_logistics

ቁጥር _____
Ref.No
ቀን _____
Date

2. ብሔራዊ ታሪፍ ቁጥር 3208.9010 የዕቃ አይነት መግለጫ በሚከተለው ተተክቷል፤

አንቀጽ (1)	የኤች ኤስ ኮድ (2)	የታሪፍ ቁጥር (3)	የዕቃው ዓይነት (4)	የመስፈሪያው አይነት (5)	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ (6)
32.08	3208.90	3208.9010	---ላክርስ (አድሄሲቭ፣ ፕሮቴክቲቭ)፣ ቫርኒሽ (ኦቨር ፕሪንት፣ ጎልድ፣ ክሊር) እና ቤዝ ኮት (ዋይት ኢናሚል፣ ባሬር) ---Lacquers (Adhesive, Protective), varnishes (over print, gold, Clear) and Base coat (White enamel, barrier)	ኪ.ግ kg	15%

3. ታሪፍ ቁጥር 4819.6000 የታሪፍ መጣኔ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

አንቀጽ (1)	የኤች ኤስ ኮድ (2)	የታሪፍ ቁጥር (3)	የዕቃው ዓይነት (4)	የመስፈሪያው አይነት (5)	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ (6)
48.19		4819.6000	-የሩይል መያዣ ሳጥኖች፣ የደብዳቤ ማዘዋወሪ ትሪዎች፣ ማከማቻ ሳጥኖችና ተመሳሳይ ዕቃዎች በቢሮዎች፣ በሱቆች ወይም በተመሳሳይ ቦታ የሚያገለግሉ - Box files, letter trays, storage boxes and similar articles, of a kind used in offices, shops, or the like	ኪ.ግ kg	35%

4. ታሪፍ ቁጥር 4821.1000 የታሪፍ መጣኔ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

አንቀጽ (1)	የኤች ኤስ ኮድ (2)	የታሪፍ ቁጥር (3)	የዕቃው ዓይነት (4)	የመስፈሪያው አይነት (5)	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ (6)
48.21		4821.1000	- የታተመ - Printed	ኪ.ግ kg	35%

5. ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የተበተኑ አካላትን ከውጭ ሀገር በማምጣት ይገጣጥሙ የነበሩ ነገር ግን ለዕቃው ከተቀመጠው የመጨረሻ የመበተን እና የመገጠም ደረጃ ከፍ ያለ የእሴት ጭማሪ የሚያደርጉ ገጣጣሚዎች/አምራች ኢንዱስትሪዎች አምራች መሆናቸውን የሚያሳይ የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃድ፣ የግዥ ደረሰኝ፣ የዕቃ ማሸጊያ ዝርዝር እና የማስጫኛ ሰነዶች በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል ለገንዘብ ሚኒስቴር እያቀረቡ የታሪፍ መጣኔያቸው በከፊል ለተበተነ ወይም ሙሉ በሙሉ ለተበተነ ዕቃ ከተቀመጠው ከፍ ያለ ከሆነ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለተበተኑ ዕቃዎች

Ministry of Finance ARCHIVES
በኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ማኔጅመንት ቁጥር 1 No 1 Ethiopian Customs Commission Records Document Management

ቁጥር _____
Ref.No
ቀን _____
Date

በተቀመጠው የታሪፍ መጣኔ መሰረት ወይም መጣኔያቸው ከተቀመጠው መጣኔ በታች ከሆነ ደግሞ ለግብዓትነት የመጡት ዕቃዎች በራሳቸው የታሪፍ መደብ ተመድበው በተቀመጠላቸው የታሪፍ መጣኔ መሰረት እንዲስተናገዱ እንዲደረግ፤ይህ ተፈፃሚ አእንዲሆን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የግብዓት

ምርት ጥምርታ አዘጋጅቶ እንዲያቀር እንዲሁም አፈፃፀሙን እየተከታተለ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት እንዲያቀርብ፤

6. ታሪፍ ቁጥር 8516.6000 በብሔራዊ የታሪፍ ቁጥር ተከፋፈል በሚከተለው ተተክቷል፤

አንቀጽ (1)	የኤች ኤስ ኮድ (2)	የታሪፍ ቁጥር (3)	የዕቃው ዓይነት (4)	የመስፈሪያው አይነት (5)	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ (6)
85.16	8516.60	8516.6010	--- በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠም ሙሉ በሙሉ ተበትኖ የቀረበ ---Presented CKD for the assembly industry	U ቁጥር	15
		8516.6020	--- በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠም በከፊል ተበትኖ የቀረበ ---Presented SKD for the assembly industry	U ቁጥር	25
		8516.1090	--- ሌሎች --- Others	U ቁጥር	35

7. ታሪፍ ቁጥር 9405.1100 በብሔራዊ የታሪፍ ቁጥር በመከፋፈል በሚከተለው መልኩ ተሻሽሏል፤

አንቀጽ (1)	የኤች ኤስ ኮድ (2)	የታሪፍ ቁጥር (3)	የዕቃው ዓይነት (4)	የመስፈሪያው አይነት (5)	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ (6)
94.05	9405.11		-- ከብርሀን ፈንጣቂ ዲዮዶች (ኤልኢዲ) በሚገኝ ብርሀን በብቸኝነት እንዲሠሩ ዲዛይን የተደረጉ፦ -- Designed for use solely with light-emitting diode (LED) light sources:		
		9405.1110	--- ሙሉ በሙሉ የተበተነ --- CKD	ኪ.ግ kg	15
		9405.1190	--- ሌሎች --- Others	ኪ.ግ kg	25

https://t.me/sirius_logistics

Ministry of Finance ARCHIVES 6

ቁጥር 1 No 1 Records Directorate

ቁጥር _____
Ref.No
ቀን _____
Date

8. የቀላል ፈሳሽ ፓራፊን ኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት፡- በተለያዩ ጊዜያት በጉምሩክ ኮሚሽን ለቀረቡ ጥያቄዎች በመስሪያ ቤታችን

ሀ. በቁጥር ማኢ 30/7/10719 በቀን 17/11/2015 እና

ለ. በቁጥር ታፖመ/ነ/578/16 በቀን 5/4/2016 በተፃፉ ደብዳቤዎች ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ችግሩ ሊቀረፍ አለመቻሉ ተገልጿል፡፡

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 እንዲሁም በተሻሻለው አዋጅ በታሪፍ ቁጥር 2710.1940 እና 2710.2040 የሚመደቡ ፈሳሽ ፓራፊኖች ኤክሳይዝ ታክስ ከሚመለከታቸው ዕቃዎች ዝርዝር ስር

አልተካተቱም፡፡ ስለሆነም በታሪፍ አመዳደብ ስርዓቱ በታሪፍ ቁጥር 2710.1200 ቀላል ዘይቶችና ዝግጅቶች በሚል ከሌሎች ዕቃዎች ጋር ተቀላቅሎ የተመደበ ቢሆንም ከኤክሳይዝ ታክስ አንፃር በታሪፍ ቁጥር 2710.1940 እና 2710.2040 ከተመደቡ ፓሪፊኖች የተለየ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከታሪፍ አመዳደብ ጋር የተያዘ ችግር ስለሆነ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 67/2013 አንቀፅ 40 ለገንዘብ ሚኒስቴር ከጉምሩክ ታሪፍ አመዳደብና ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር የተያያዘውን ሰንጠረዥ ተጣጥመው ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የሚያስችል ማብራሪያ ሊያወጣ እንደሚችል በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቀላል ፈሳሽ ፓራፊን ኤክሳይዝ ታክስ እንደማይመለከተው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

በመሆኑም የተደረጉ ማሻሻያዎች እና ማስተካከያዎች ይህ ደብዳቤ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከአምስት የሥራ ቀናት በኋላ ተቀባይነት በሚያገኙ የጉምሩክ ዲክላራሲዮኖች ላይ ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

https://t.me/sirius_logistics

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶር.)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-
ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ቁጥር 1
No 1